# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 1-3 ልዩ እትም መስከረም / ህዳር 1990

## ከአዘጋጅ ብዕር

መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ሥርጭቱን የጀመረው የቀስተ ደመና ሬዲዮ፤ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ የአራት ወራት የአገልግሎት ግዜውን አጠናቅቆ አምስተኛ ውን ወር ሊይዝ ነው።

የቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚያስተላልፋቸው ዜናዎች ፤ ትችቶችና ትንተናዎች ፤ ቃለ መጠይቆች ወዘተ በአየር ላይ ውለው ሳይጨበጡ እንደተበተኑ የትም እንዳይቀሩና በፅሁፍ ተቀርፀው ቢቀመጡ ለተደራሲው የሚሰጡት ጥቅም የላቀ ይሆናል ብለን በማሰብ ፤ ከወራት በፊት አንድ መፅሄት ለመጀመር አቅደን ጊዜ ጊዜን እየወለደ ዛሬ ላይ ደርሰናል።

ባለፉት አራት ወራት ቀስተ ደመና ሬዲዮ ያስተላለፋቸውን ትችቶችና አስተያየቶች በማቀናበር ይህንን 'ልዩ እትም' አዘጋጅተናል። የተለያዩ ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት የሰጡት እነዚህ አስተያየቶች በርካታ ቁም ነገሮች ያስጨብጣሉ የሚል ዕምነት አለን።

የ 'ቀስተ ደመና' ጋዜጣ ከዚህ ልዩ እትም በኋላ በየግዜው እንደሚወጣ ልናበስር እንወዳለን።

መልካም ንባብ !

ቀስተ ደመና ሬዲዮ የሚተላለፍበት ፕሮግራም ገጽ....................................19

* የኢሃዴግን ጦር ጠማሽ አቋም ላለማገዝ...........
ሰላማዊውን የፖለቲካ ትግል አለማፍዘዝ.......................................4

* የቡድን ውኽንብር ጠቃሚነቱ ለአምባገነኖች ብቻ ነው ................10

* ከፓሪሱ ጉባዔ ያልተቀሰመው ትምህርት..................................3

* ከዶላር ወይስ ከናቅፋ ከጽድቅ ወይስ ከኩነኔ....................9

* ለብቸኛው ልዕለ ኃያል የሚሳነው ነገር አለ ለካ ሄ ሄ.....13

* በነ ዶር ታዬ ላይ በሃሰት አልመሰክርም በማለት ራሳቸው በሃሰት የተወነጀሉት ....................15

* ከባሻገሩ ሽግግሩ እንዳያስቸግር..18

* ለነፃ ምርጫ አመች የኃይል ሚዛን መታገል አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ..................................................6

አስተያየት፤ ትችት፤ ወዘተ ካላችሁ አድራሻችን እንደሚከተለው ነው፤
Radio Rainbow
c/o P.O.Box 140104
53056 Bonn , Germany . Fax : 0049 228 612381

GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA
Groupe de Recherche et d'Action pour la pain en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique
Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa
ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

እንግዲህ የፓሪሱ ጉባኤ ትምህርት ግልጽ ነበር። ግልጽና ደሞክራሲያዊ የሆነ የጋራ ዓላማ ይዞ በጋራ በጋራ መነሳት ምንግዜም ቢሆን ወሳኝ የሆነውን የሕዝብ የትግል ሞራል ከፍ እንደሚያደርግና ወደ ድልም እንደሚያመራ ፤ በአለም አቀፍ ደርጃም ቢሆን ከዳር እስከ ዳር ከበሬታንና ድጋፍን እንደሚያስገኝ በማያሻማ ሁኔታ አይተናል። የኢትዮጵያ ሰላም ደሞክራሲና የህዝቦችዋ አንድነት ጉዳይ ያንገበግበናል የሚሉ ኃይሎችና ድርጅቶች ከዚህ ሁሉ ቀላሉንና ተገቢውን ትምህርት መቅሰም ነበረባቸው። አልቀሰሙም።

በየድርጅቶቹ አመራር ላይ ያሉት ታጋዮች በፖለቲካ በመጣ ነገር የዝንብ ጠንጋራ ለመለየት የሚያስችላቸው የትግል ልምድ አካብተዋል ብለን ስንገምት በአልባሌ የከፋፋዮች ወጥመድ ተመልሰው ተዘፈቁ። የተቀሰቀሰው የህዝብ ተስፋ ከሰመ። የተገኘው የዲፕሎማስያዊ ድል ተመልሶ ደብዛው ጠፋ። ተቃዋሚዎች በጋራ ይዘውት የነበረውን የፖለቲካና የዲፕሎማሲያዊ አጥቂነት ከለቀቁና ከሰደዱና ሁሉም አስቸጋሪ የሆነ የተከላካይነት ማጥ ውስጥ ከወደቁ በኋላ፤ አሁን ይህንን አጥቂነት በይግላቸው በማሳደድ ትግል ላይ ይገኛሉ።

በዚህ መልክ የሰላምና የዴሞክራሲ ኃይሎች ዛሬ ለሚገኙበት አስቸጋሪ ሁኔታ ሺ ምክንያቶች መደርደር ይቻላል። የጋራ አቋም ወይም የትግል ህብረት መጥፋት የሚባል ሰ በብ ግን ከነዚህ ውስጥ ሊደመር የሚችል ምክንያት አይደለም። የትግሉ መዳከምና መዝረክረክ የምያንገበግባቸው ዜጎች ሁሉ ይህንን እንዲገነዘቡና በያለበት ለትግል አንድነት የተቻላቸውን ግፊት እንዲያደርጉ የሰባቱ ድርጅቶች ተወካዮች ተስማምተው ያቀረቡትን ሰነድ ዋና ዋና ይዘቶች በአጭር በአጭሩ እየተነተንን ለአድማጮቻችን በግዜው ለማቅረብ እንሞክራለን////

## የእህዴግን ጦር ጠማሽ አቋም ላለማገዝ ፡ ሰላማዊውን የፖለቲካ ትግል አለማፍዘዝ

መስከረም 22 1990

ዛሬ በሃገራችን በአንድ በኩል ጸረ ህዝብና ጦር ጠማሽ ኃይሎች፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሰላምና የደሞክራሲ አማራጭ የሚያቀርቡ ሃይሎች ተፋጥው ይገኛሉ። ማን ጦር ጠማሽ ማን ሰላም ወዳድ እንደሆነም ግልጽ ይመስለናል።

የኢህአዴግ አመራር ፡እንኳን በሺ የሚቆጥሩ የሽምጥ ተዋጊዎች ድፍን ኢትዮጵያ ጦር ቢያነሳብኝ በአሸናፊነት እወጣለሁ ፡ በሚል የቅዠት ዓለም ውስጥ የሚዋዥቅ ልቡ ያበጠ አጥፊ ሃይል ነው ። በዚያው ልክ ደግሞ ሰላማዊ የፖለቲካን ትግል ከጦር የሚፈራ፤ የውይይትን ጥሪ ከጦር ክተት አዋጅ መለየት የማይችል ፤ ውይይትና ድርድር አጉል ግዜ ማጥፋት የሚመስለው እጅግ ኋላ ቀርና
የፖለቲካ ድንኮች የተጠራቀሙበት አመራር ነው።

የኢህአዴግ አመራር ካለበት የፖለቲካ ክሥረት የተነሳ በኢትዮጵያ ህዝቦችም ፊት ሆነ በአለም አቀፍ ደጋፊዎቹ ፊት ከሃገራችን ደሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር የፖለቲካ ትግል የሚፈልግም የሚችልም ሃይል አይደለም። ግልጽና ደሞክራሲያዊ ጥያቄ አንስቶ አዲስ አበባ ሰልፍ ከሚወጣበት ዘጋ ይልቅ በሃገራችን ገጠሮች መቶ ሺ ጦር ገጥሞት በሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች እርስ በርስ የሚተላለቁበትን ግጭት ይበልጥ የሚመኝ አመራር ነው። ሌላውን ሁሉ የትግል ስልት ትቶ እንዲህ አይነቱን እልቂት መጋበዙ እንደማንኛውም በህዝብ እምነት የሌለው ኃይል ሌላ የትግል አማራጭ ስለማይታየው ነው።

በሃገራችን ደሞክራቶች ሰፈር ያለው ስዕል ግን ከዚህ ጨርሶ የተለየ ስዕል ነው። ከኢህአዴግ በተቃራኒ የኃገራችን የሰላምና የዴሞክራሲ ኃይሎች የማያጠራጥር የህዝብ ድጋፍና ማንም የማይክደው የፖለቲካ የበላይነት አላቸው ። ይህንን የበላይነት እንዳይነጠቁ እስከሰሩና እስካንከባከቡት ድረስ የትግል ስልት ምርጫቸው ከአሸዋ የበዛ ነው።ኢህአዴግ የሰላማዊ ፖለቲካ ትግልን በር ለመዝጋት በሚያደርገው ሙከራ የተነሳ እሳትን በእሳት ብለው እሱው በመረጠው የትግል ስልት የሚፋለሙት ታጣቂዎች ይኖራሉ። ግፍና ጭቆና እየተበራከተ ሲሄድ አንድ ህብረተሰብ እንዳለ ዘላለሙን እጁን ይሰጣል ብለን ስለማናምን እንደዚህ አይነት ግጭቶች እየተበራከቱ እንደሚሄዱ መጠራጠር አይቻልም። ግን ደግሞ የኃገራችን የሰላምና የደሞክራሲ ኃይሎች ይህንን አጥፊ ኃይል እሱው ያዋጣኛል ብሎ በህብረተሰቡ ላይ በጫነው ስልት ብቻ አይገጥሙትም። ህገ መንግሥቱን ተቀብለው እሱ ደነገገ የተባለውን መብት አንቀፅ በአንቀፅ እየጠቀሱ የኢህአዴግን መንግሥት በገዛ ህጉ ለመፋለም የሚመርጡ ኃይሎች አሉ። ህገ መንግስቱን በይዘቱም ሆነ በአጸዳደቁ ሂደት ተቃውመው በሰላማዊና ህጋዊ ዘዴ የሚታገሉ ዜጎች አሉ። ለዚሁ ዓላማም ሰላማዊና የኅቡዕ የትግል ስልት መርጠው በዚያም በኩል ለመሰማራት የሚገደዱ ኃይሎች አሉ። ባጭሩ የትግል ስልት ምርጫ የማይኖረው ጸረ ህዝቡ ኃይል ብቻ ነው።

ለዚህ ነው በአርእስታችን ኢህአደግ ወጥመድ ውስጥ ላለምግባትና ጦር ጠማሽ አቋሙን ላለማገዝ የሰላሙን የፖለቲካ ትግል ያለማፍዘዝ ያልነው። በኛ እምነት እነኢህአደግ ይህንን የትግል ስልት የጥቂት ህልመኞች ቅዠት አርገው ሊያቀርቡት ቢሞክሩም ፤ እንዳይስፋፋና እንዳያጥለቀልቃቸው በሚወስዷቸው የጭቆና እርምጃዎች የተነሳ የሚከፈለው መስዋዕትነት እየተበራከተ ቢሄድም ሰላማዊው የፖለቲካ ትግል የሃገራችን የወደፊት እድል ሲወሰን ወሳኝ አስተዋጽኦ ሊኖረው የሚችል የትግል ስልት ነው።

በዚህ ከራስ ጸጉር የበዙ የፖለቲካ ፤ የሶሻል፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍትህ ችግሮች በሚጨፍሩበት ህብረተሰባችን ይህ የፖለቲካና የዲፕሎማሲያዊ ትግል መስከ ተሟጦ አልቋል ፤ በሩ ሁሉ ተዘግቷል በሚል ሰበብ እንዳደበዝዝ ከተደረገ የሚያመለክተው አንድ ነገር ቢቻ ይሆናል። ይኸውም የደሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ኃይሎች የፖለቲካ አጥቂነትና የበላይነት ተሟጦ ማለቁንና ከከሳራው ኢህአደግ እኩል ወርደው መገኘታቸውን ነው። በእርግጥም እንደዚህ ከሆነ ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ እጅግ አስከፊ የሆነ ውዥንብርና አቅጣጫ ማጣት፤ አደገኛ የሆነ ለጸረ ህዝቦች ብቻ የሚያመች ተስፋ መቁረጥና የሞራል ውድቀት ሰፍኗል ማለት ነውና የተቃዋሚ ኃይሎች ዋና ተቀዳሚና አንገብጋቢ ተግባር ይህንን ያጡትን የበላይነትና አጥቂነት መልሰው ለመጎናጸፍ ያልተቆጠበ ጥርት ማድረግ ይገባቸዋል። ይህንን ታሪካዊ ሃላፊነት በመወጣት የፖለቲካ ድርጅቶች በየለቱ ለመብቱ ፤ ለክብሩና ለህልውናው የፖለቲካ ትንንቅ የያዘውን ህዝብ በግንባር ቀደምነት መምራት ካልቻሉ የሃገራችን ነገር የሚሸሹበት ምሽግ ሲሸሽ ታየ እንደተባለው መሆኑ ነው።

ይህን ሁሉ ስንል ሰላማዊውን ትግል ለማፋፋም ምን ያህል እንቅፋቶች እንዳሉ አጥተነው አይደለም።

ባለፉት ሁለት መቶ አመታት የ አስር ዓመት እድሜ አጠቃላይና ቀጣይነት ያለው ሰላም ባላየ ህብረተሰብ ፤ ቢያንስ ቢያንስ ከስመ ጥፉው ዘመነ መሳፍንት እስከ ኢህአደግ ድረስ ሰላማዊ የሆነ የስልጣን ሽግግር ባልታየበት አገር ሰላማዊ ትግል ሲባል ፥እጅ ስጡ፥ የሚል የአዘናጊዎች ተንኮል ወይም ደግሞ የወኔ ቢሶች ጥሪ ሊመስል ይችላል። ግን ደግሞ በህቡእ ተካሄደ በይፋ ሰላማዊ ትግል የጀግንነት ትግል ነው። ለማራመድ የሚጠይቀው ቆራጥነትና ሲካሄድ የሚጠይቀው መስዋእትነት ከጦር ሜዳ ፍልምያ የሚተናነስ ላለመሆኑ ዛሬ በዚህ ትግል ተሰማርተው ለእስር፤ ለግድያ፤ ለአፈና እየተዳረጉ ቤት ንብረታቸው የተፈታ ዜጎች ህያው ምስክሮች ናቸው።

ሌላው ችግር ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል እጅግ አሸጋሪና ውስብስብ መሆኑ ነው። ለጦር ትግል የጦር አካዳሚዎች አሉ። ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ማሰልጠኛ አካዳሚ የለውም። እንደህብረተሰቡ ተጨባች ሁኔታ ፤ እንደታሪካዊ የእድገት ደርጃው፤ እንደተጫነበት አገዛዝ፤ እንደአካባቢውና ዓለም አቀፍ የሃይል ሚዛን ወዘተ ከአሸዋ የበዙና በየግዜው ተለዋዋጭ የሆኑ መመዘኛዎችን አደበላልቀው እየተነተኑ ፤ በመጽሓፍ የሌለ በትግል ልምድ ብቻ እንጂ በስልጠና የማይገኝ ከፍተኛ የፈጠራ ችሎታን የሚያሳዩ መሪዎች ያስፈልጉታል።

ዛሬ በኢህአደግ ቁጥጥር ስር በወደቀችው ሃገራችንም እነዚህ ችግሮች አላንስ ብለው ሌሎችም አሉብን። ከውይይት ይ የጦር ፍልምያ የሚመርጥ እብሪተኛ ኃይል እስካለ ድረስ ፤ በገጠሮች መሣሪያ ይዘው ከሚፋለሙት ዜጎች ይልቅ የከተማ ሰላማዊ ሰልፎችን ይበልጥ የሚፈራ አገዛዝ እስካለ ድረስ ፤ ሰላማዊ ተቃውሞን ከጦር በመፍራቱ የተነሳ ከከተት አዋጅ ለመለየት የማይችል እውርና ኋላ ቀር አገዛዝ እስካለ ድረስ ፤ ከባሩድ ይልቅ ብዕር እያስበረገገው ጋዜጠኞችን በማሰር የዓለምን ክብረ ወሰን የያዘ ኃይል የበላይነትን እስከያዘ ድረስ ፤ በውጭ አሳዳርዎቹ ፊት ደሞክራሲን አስፍኜ የህዝብ ተቀባይነት አግኝቻለሁ እያለ የሚለፍፈው በሬ ወለደ ወሬ በሰላማዊ የከተሞች ትግል ገደል እንዳይገባበት ሌት ተቀን የሚባንን መንግሥት እስከገዛን ድረስ ያይል ይስፋፋ የምንለው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ምን ያህል ያቀበትና የመስዋእትነት ጉዞ እንደሆነ እናውቃለን

ዛሬ በትጥቁም ሆነ በሰላማዊው ትግል መስከ ይህ መስዋእትነት እየተከፈለ ነው። የዚህን መስዋእትነት እድሜ ማሳጠርም ሆነ ፍሪያማነት ለማረጋገጥ የሚቻለው በአንድ ዘዴ ብቻ ነው። ተቃዋሚ ኃይሎች የዛሬ አራት አመት ይዘውት የነበረውን የፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ አጥቂነት እንደገና በጋራ ለመጎናፀፍ የሚችሉበትን ዘዴ መሻት አለባቸው። ለዚህ መንደርደርያ የሚሆን ባለፍው ዝግጅታችን የጠቆምነው የፓሪሱ 7 ድርጅቶች የተስማሙበት በኋላም የአዲስ አበባው ጉባኤ የተቀበለው

አታጋይ ሰነድ አለ። በዚህ ሰነድ መንደርደርያነት በድርጅቶች መሃከል በተለይ ደግሞ በየድርጅቶቹ አባላት መሃከል ውይይት እንዲካሄድ ፤ ከዚያም አልፎ የትግሉ አንድነት ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ዜጎች በሙሉ እንዲመረምሩት ከሚቀጥለው ዝግጅታችን ጀምረን ለአድማጮቻችን እናቀርበዋለን።

ድረስ ያይል ይስፋፋ የምንለው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ምን ያህል ያቀበትና የመስዋእትነት ጉዞ እንደሆነ እናውቃለን

ዛሬ በትጥቁም ሆነ በሰላማዊው ትግል መስክ ይህ መስዋእትነት እየተከፈለ ነው። የዚህን መስዋእትነት እድሜ ማሳጠርም ሆነ ፍሪያማነት ለማረጋገጥ የሚቻለው በአንድ ዘዴ ብቻ ነው። ተቃዋሚ ኃይሎች የዛሬ አራት አመት ይዘውት የነበረውን የፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ አጥቂነት እንደገና በጋራ ለመጎናፀፍ የሚችሉበትን ዘዴ መሻት አለባቸው። ለዚህ መንደርደርያ የሚሆን ባለፍው ዝግጅታችን የጠቆምነው የፓሪሱ 7 ድርጅቶች የተስማሙበት በኋላም የአዲስ አበባው ጉባኤ የተቀበለው
አታጋይ ሰነድ አለ። በዚህ ሰነድ መንደርደርያነት በድርጅቶች መሃከል በተለይ ደግሞ በየድርጅቶቹ አባላት መሃከል ውይይት እንዲካሄድ ፤ ከዚያም አልፎ የትግሉ አንድነት ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ዜጎች በሙሉ እንዲመረምሩት ከሚቀጥለው ዝግጅታችን ጀምረን ለአድማጮቻችን እናቀርበዋለን።

# ለነፃ ምርጫ አመች የኃይል ሚዛን መታገል ዛሬም አንገብጋቢ ጥያቄ ነው

መስከረም 29 ፥ 1990

ባለፈው ዝግጅታችን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች ከ 4 ዓመታት በፊት በጋራ ይዘውት የነበረውን የፖለቲካና የዲፕሎማሲ የበላይነት በማጣታቸው ሃገሪቱ፤ ህዝቦቿና ታጋይ ኃይሎቿ ለኢህአደግ ብቻ የሚያግዝ ከፍተኛና አደገኛ ውዥንብር ውስጥ መውደቃቸውን ጠቁመናል ። በሌላ ዝግጅታችን ደግሞ በጋራ ይዘው የነበረውን የበላይነት በገዛ እጃቸው ከሰደዱ በኋላ መልሰው ለመጎናፀፍ በየግላቸው የማሳደድ ተግባር የትም እንደማያደርሳቸው ለማስገንዘብ ሞክረናል። በዚህ ዝግጅታችን ለዚህ ችግር ዋና ምክንያት የጋራና አታጋይ መድረክ መጥፋት እንዳይደለ አውስተን የፓርሱ 7 ድርጅቶች፤

1ኛ ስለሽግግሩ ዴሞክራሲያዊ ሂደት
2ኛ ስለሽግግሩና የህገ መንግሥት ጥያቄ
3ኛ ስለብሄሮች መብትና የኢትዮጵያ አንድነትና የልእልናዋ ጉዳይ
4ኛ ስለሰላምና ዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች የትግል ትብብር ጉዳይ

ተወያይተው የተስማሙበትን ሰነድ መልሰን ለውይይት ለማቅረብ ቃል ገብተን ነበር።

በዚህም መሠረት በዛሬው ዝግጅታችን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በምን ፥ወሳኝ ጥያቄ፥ ዙሪያ በጋራ መቆምና መታገል እንዳለባቸው ፤ ይህንን ትግልም ለማስተባበር መፈጠር ስላለበት አካል ያሰፈሩትን ካቀረብን በኋላ አስተያየታችንን ለሰባቱ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት፤ ከነሰ-ም ባሻገር በሚሊዮን ለሚቆጠሩት ታጋይ ዜጎችና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እናቀርባለን።

በዚህ ጥያቄ ላይ ሰባቱ ድርጅቶች ያሰፈሩት ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ነው።

## የሰላምና ዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች የትግል ትብብር ጥያቄ

በኢትዮጵያ ሰላም ወርዶ ዘላቂ እንዲሆን ፤ የዴሞክራሲ መሰረት ተጥሎ በሱ ላይ አዲስ ስርዓት እንዲገነባ ለሕብረተሰቡ መሰረታዊ ችግሮች አማራጭ መፍትሄዎች አቅርቦ በደሞክራሲያዊ ምርጫና በህዝብ ድጋፍ ከሥራ ላይ ለማዋል ሰፋ ያለ ውክልና ያለው መንግስት በአገሪቱ ዛሬ የልም።